# ቁጥሮች ምን ይላሉ!!! ምናባዊ ትንተና

ብርሃነመስቀል ወልደገሪማ አፅብሃ, aberhaneth@gmail.com,

ከጎንደር ከተማ

ጥር 30 2002ዓም

ውድ አንባቢያን በድጋሚ በዚህች ሁለተኛዋ ፅሁፌ ወደ 80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር በመጠቀም የሚያመጣው ውጤት በመመልከት ምናባዊ ትንተና የያዘች ጽሑፍ ይኸውና ቢያለሁ:: መልካም ንባብ እመኛለሁ::

ወደድንም ጠላንም ህዝብ ሃይል ነው ቻይናን እዩ (ተጨማሪ ሌላ ነገርም ቢኖራቸው):: ህዝብ ቆራጥና ብልህ መሪ ሲኖረውና ህዝቡም ለጠርነት ማቁን ጨርቁን ሳይል ለአገር ዳር ደንበሩ እንደሚዘምተው ሁሉ ለልማትም ከዘመተ ህዝብ ልማት ነው:: ህዝብ የአገር መለያና መኩሪያ ሀብት ነው (ለህዝብና የህዝብ ድንቅ ውጤቶችን ለማየት በቱሪስት መልክ ሰው ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር እየተመመ እያየነው ነውና):: ስለህዝብ ይህን ካልኩ ዘንዳ የህዝብ ቁጥር መሰረት የተሰላ ሂሳብ ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል::

ልብ በሉ 80 ሚሊዮን ህዝብ ሁሉ የአምራችነት እድሜ ያለ ማለት አይደለም:: ሆኖም ግን በአምራችነት እድሜ ያለ ህዝብ አምራች ላልሆኑ ክፍሎችን (ህጻናትና ሽማግሌዎች) ጨምረው ይሰራሉ ተብሎ ታሳቢ ተደርጓል:: ህዝብ እንደ አንድ ለድህነት ከዘመተ በጥቂት ዓመታ ኢትዮጵያ ከድህነት ትወጣለች::

## ጉዞ ፩

| | |
|---|---|
| ቁጥር: | 80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ |
| አበረከተ (ብር): | እንደምንም ተጣጥሮ እያንዳንዱ ሰው በቀን አንድ ብር |
| ጠቅላላ የተበረከተ (ብር): | • በቀን: 80ሚሊዮን ብር<br>• በወር: 2.4ቢሊዮን ብር<br>• በ6ወር:14.4ቢሊዮን ብር<br>• በዓመት: 29.2ቢሊዮን ብር |

**የተበረከተው የዋለበት አላማ**

በዓመት የተበረከተው ገንዘብ ቢያንስ ቢያንስ አንድ የውሃ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ለመገንባት የሚያስችል የገንዘብ አቅም ይኖራል ማለት ነው:: ልብ በሉ ከእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ህዝብ የወጣች ገንዘብ ባንዴ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ መስራት ተቻለ ማለት ነው በአንድ አመት ይህ 80ሚሊዮን ህዝብ አንድ የውሃ ኤሌክትሪ ሃይል ማመንጨት ከቻለ በሁለት ዓመት ሁለት የውሃ ኤሌክትሪ ሃይል በሶስት ዓመት...... (ይህን ስል የመገንቢያ ጊዜ ሳይጨምር ነው::)

እሺ ሃይል ማመንጫው በመንግስት በጀት ይሰራ ቢባል ይህን ከህዝብ የተሰበሰበ ገንዘብ በአንዴ በያንዳንዱ የአገራችን ዋና ዋና ከተሞች ልዩ የሆኑ የቤት መጻህፍት ቤቶች መገንባት ይቻላል ወይም ትላልቅ ፋብሪካዎች በየክልሉ አንድ አንድ መገንባት ይቻላል:: ይህም በፋብሪካዎች ውስጥ በዛ ያለ ሰው ሃይል የስራ እድል ተፈጠረ ማለት ነው ተባብረን እንደ አንድ ለልማት ከተነሳን ይህን ያህል ስኬት ማግኘት ይቻላል:: እያንዳንዱ የህብረተሰብ ክፍልም ተጠቃሚ ያደርጋል::

**ጉዞ ፪**

| ቁጥር | 80ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ |
|---|---|
| አበረከተ (ነጻ ጉልበት) | በወር አንድ ቀን ነፃ የጉልብት ስራ መስጠት (ጽዳት ፣ ችግኝ ተከላ ወዘተርፈ) |

**የተበረከተው የዋለበት አላማ**

1. **ጽዳት**

ከተሞቻችን እንዲሁም አከባቢያችን ፅዱና ከበሽታ ማስተላለፊያ ከመሆን ነፃ ይሆናሉ:: ህዝባችን ለበሽታዎች ህክምና የሚያወጣቸው የመድሃኒትና የተለያዩ የጤና አገልግሎቶች ወጪዎች ቀነሰ ማለት ነው:: ከተሰበሰው ቆሻሻ ለባዮጋዝ ምርት ግብዓት ይሆናል:: አንዳንዶቹም ለፋብሪካዎች እንደጥሬ ዕቃ (ጠርሙዝ ወረቀት ጎማ ወዘተ) ሊሆኑ ይችላሉ:: በአንድ ድንጋይ ሁለት...መቶ ወፎች... ማለት ይህ ነው ለካ!!! (የአከባቢና ጥበቃ ድህንነት እንዳይቀየሙ መግደል መምታት የሚለው አልጨመርኩም)

2. **ችግኝ ተከላ**

እያንዳንዱ 80ሚሊዮን ህዝብ በቀን አንድ ችግኝ ቢተክል በቀን 80ሚሊዮን፣ በወር 2.4ቢሊዮን፣ በ6ወር 14.4ቢሊዮን፣ በዓመት 29 ቢሊዮን ችግኝ ይተከላል ማለት ነው::

ችግኝ ተከላ ስል ቀጥታ በአይኔ ድቅን የሚልብኝ አገራችን በደን ስትሸፈንና የከባቢው አየር ቀዝቀዝ የሚል ስሜት ሲሰማኝ ነው:: ይህን የደን መሸፈን ከላይ በአውሮፕላን አገራችን ስናያት ከባንዴራችን ቀለማት መካከል በአ-ረ-ን-ጓ-ዴ ቀለም አሸብርቃ እናያታለን:: የባንዴራችንም መልእክት ወይም ትርጉም በተግባር አሳየን ማለት ነው:: በተጨማሪም በአገራችን የንጹህ አየር ምርት በሽበሽ ይሆናል:: በዚሁም ጤነኛ የአየር ንብረት ይኖረናል:: አገራችንም ምቹ የቱሪስት መስህብ ትሆናለች:: **የኢትዮጵያ ወንዞችም ቀድሞ ውሃ ከማስተላለፍ ስራ ቦዝነው ከነበሩበት በዚህ ጊዜ የሚጠበቅባቸው ስራ ይሰራሉ::** ሃይቆች ውሃ ማቆር የተፈጥሮ ስራቸው በአግባቡ ይወጣሉ:: እንዲሁም የውሃ ግድቦች ከዓመት ዓመት ሙሉ ይሆናሉ:: ለሃይል ማመንጨትም ሆነ ለመስኖ፣ ለዓሳ እርባታ፣ ለቱሪስት መስህብነት ግዴታቸውን ይውጣሉ:: በነገራችን ላይ የሃይል ማመንጫ ግድቦቻችን ሙሉ ስለሚሆኑ በውሃ ሃይል የሚመረት የኤሌክትሪክ ሃይል በአስተማማኝነት ይጨምራል:: መብራት መጥፋት ድሮ ቀረ ተብሎ ይሰለቃል:: ባለፈው ዓመት በወዲያኛው ወዲያኛው ዓመት መብራት የመጥፋት ጠስ ምን ያህል ችግሩ በየቤታችን በር እንዳንኳኳ እንዲሁም ማንኳኳት ብቻ ሳይሆን በቤታችን ውስጥ ዘው ብሎ በመግባት ኢኮኖሚ በሉት ሌላ እንዳናጋ እናውቀዋለን:: ለምሳሌ ቆንጠር አድርጎ ለማሳየት ያህል የዩኒቨርሲቲ ተማሪው (ቸካዩ)፣ ካፍተሪያዎች (ለአስጠጬም ለጠጬም)፣ ጸጉር ማስተካከያ ቤቶች (ለአስተካካዩም ለተስተካካዩም)፣ ለልኳንዳ ቤቶች (ለስጋ አስበይም ለበይም) ወዘተርፈ ወዘተርፈ ቢየዋለሁ::

አርሶ አደር ህዝባችንም በመስኖም ሆነ በዝናብ ውሃ በሚያገኘው ምርቱ ይጨምራል:: አርሶ አደሩ የተግበሰበሰ ምርት ያመርታል ይሸጣል:: ከተሜውም በመካከለኛ ዋጋ ሸምቶ ይበላል:: በአጠቃላይ አገራችን የሮኬት ያህል ፍጥነት የምታድግ ሁኖ ይሰማኛል::

**ማጠቃለያ**

ከላይ የተጠቀሱት እንደምሳሌ ለማቅረብ ታስቦ እንጂ ህዝብ እንደአንድ ቆሞ ከተሰለፈ የማይገነድሰው የችግር ተራራ የለም እንዲሁም ማደግ መመንገድም ይችላል:: ችግኝ ተከላ ይህን ያህል ውበት፣ ጤና፣ እድገትና ብልጽግና ያለው ከሆነ በአንድ ልብ ይህን ቅዱስ ሃሳበ በተግባር እንግለጸው እደግመዋለሁ በተግባር እንግለጸው:: ለዚሁ ቅዱስ ተግባር ቆርጠው ለተነሱ ዜጎቻችንም የሞራል፣ የጉልበት፣ የገንዘብ ድጋፍ እንስጣቸው እላለሁ:: በኢትዮጵያ አገራችን በህብረት የሚሰሩ ስራዎች በጥናት ተለይተው በግልጽ ህዝቡ እንዲያወቃቸው ይደረግ:: ህዝብም የሚያስተባብር ተቋም ይቋቋም የተቋቋመ ካለም በአስቸካይ ለህዝቡ የማስተዋወቂያ

መንገዶች ይፍጠር:: በቀጣይ ተመሳሳይ ጽሁፍ እስገምንገናኝ ውድ አንባቢዎቼ ደህና ሰንብቱልኝ:: ኢትዮጵያችንም ትደግ ትመንገድ!!! ባአሁኑ ዘመን ድህንት ቁስቁልናም በኢትዮጵያ ታሪክ አንዲጠፋ እመኛለሁ::

**ህብረት ጥንካሬ ነው!!!**

Unity Is Strength!!!